

የካቲት ፳፭ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም
March 4, 2011

# ከታሪክ ማኅደር

ጣሹ ገመዳ

በቅርቡ አንድ ዘመዴ የአስማሳዩን የወያኔ የቀይ ሽብር ሙዜየም ብሎ የአሠራውን ለመጎብኘት በመሄድ “አደራ መቼም እንዳይደገም!!” ልዩ እትም ግንቦት ፳፻፩ ዓ.ም የሚል መጽሔት ልኮልኛል። በዚህ መጼሕት ደረግ የፍጌል ወጠጤ ሊላቸው የፈለጋቸውን ፎቶ ግራፎቻቸውን በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም አዲስ አበባና አካባቢው እንዲሁም በየጠቅላይ ግዛቱ





ለጥፎ እንደ ነበር ብዙዎቻቸን አናውቃልን። በዚህ መጽሔት ውስጥ በሕይወት ያሉትንና የሌሉትን የያዘ ነው። እንዳጋጣሚ ጓደኛየና የትግል አጋሬ የነበረው አንዱ ማርቆስ ሐጎስ የመጽሔት አዘጋጅዎቹ ከባለቤቱ ጋር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ለማንበብ በቅቻለሁ። ቃለ ምልልሱ ከማቅረቤ በፊት ከኔ ጋር የነበረውን የትግል ቀረቤታ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፦

ማርቆስ ሐጎስና እኔ የተዋወቅነው ማኅበራችንን በሕግ ሕዝባዊ ሚኒሰቴር ካወቅለን በኋላ ነበር። ይኸውም ከታኅሣሥ ፲፱፻፷ ዓ.ም በኋላ መሆኑ ነው። ትወቅቃችን ማርቆስ በሠራተኛው ማኅበር ቀደም ብሎ ሲታገል ስለነበር ጠቃሚ ምክሮችን ይለግሰኝ ነበር። ይኸም ግኑኙነታችንን እየጠበቀ ሲሄድ ከአየር መንገድና ቀደም ብሎ ከሚያወቀቸው ጓደኛው ጋር (ቢስ ኩባንያ የሚሠራ- አሁንም በሕይወት ያለ) አብረን ለመሥራት ተስማማን። እንደሚታወቀው ሁሉ ኢሠአማ መሪዎቹን በሕጉ መሠረት መርጦ አያውቅም ነበርና ለውጥ እንደሚያሰፈልገው ያለ አንዳች አለማመንታት ተስማማን። እኛም በተቻለን መጠን ሐሳባችን የሚጋሩትንና የምናውቃቸውን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንን ማነጋገር ጀመረን። በሕጉ መሠረት በየሁለት ዓመቱ መሪዎች መቀየር ስላለባቸው አነ ፍሥሐ ጽዮን ተኬን አውርደን ከተላያዩ ማኅበራት ተወከለው ከሚመጡት መካከል ለማስመረጥ ነበር ዋናው ዓለማችን። የምረጫው ጊዜ ሰኔ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ነበርና በተቻለን መጥን አብዛኛውን መሪዎች አነጋግረናል። ነገር ግን ውይይታችን እንዲጠናከር የረዳን ዘንድ የቢስ ኩባንያው ወንደማችን ከሣሙኤል ዓለማየሁ ጋር አስተዋወቀን። ሣሙእል የቢስ ኩባንያ ሠራተኛ ነበር። የኢሠአማ መሪዎች ማኅበሩን እንደ ዕርስት ጉልታቸው አርገው ስለሚመለከቱት ምርጫ በተደረገ ቁጥር እነሱኑ መልሰው መላልሰው ይመርጧቸው ነበር። የኛ ቡድን እንዲህ ዓይነቱን አሠራር ላንዴም ለሁሌም ለመቀየር ታጠቀን ተነሳን። አምስታችንና አጋሮቻችንን ይዘን በየነ ሰሎሞንና ፍሥሐ ጽዮንና እንዲሁም የቀረቱን ጓደኞቻቸውን በሠራተኛው ወኪሎች ለመተካት ትግሉን አጧጣፍነው። ከላይ እንደጠቀስኩት ሰኔ

ከመድረሱ በፊት ለወጥ የማይፈለጉ ሰዎችን እንደነ ጣዕም የለው እሸቴንና ብጤዎቹን ጽሕፈት ቤቱ ማደራጀት ጀመረ። የኢሠአማ ባልሥልጣናት ዓላመችን እንዳይሳካ ብዙ ገንዘብ አወጥጣል ።

እኛም ከሣሙኤል  ጋር ሆነን መደረግ የሚገባቸውን ስልቶችና ዘዴዎች ልዩ ልዩ እቅዶች መተለም ጀመርን። እንደሚታወቀው ሁሉ ኢሠአማ ከሠራተኛው እሰከ ላብ አደሩ ድረስ አባላት ነበሩት። በተለይ ደገሞ የኢንዶ-ኢትዮጵያ ቴክሰታይል የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ላብ አደሮች ቁጥር ወደ አራት ሺ በላይ ይደረስ  ነበር። ብዙ አባለት ያሉት በምረጫው ጊዜ ድምጻቸውም ወሳኝ ነበር። ሻጥረኛው አመራርም ከኛ ኮሚቴ ጋር እንዳይሠሩ ከለከሏቸው ፤  እንዳይተባበሩም አደረጓቸው።

ቀኑ ደረስና ሰኔ ፲፱፻፷፬ ዓ.ም በኢሠአማ አዳራሽ የሁለት ቀን ስብሰባ ተጠራ። የመጀመሪያው ቀን ማኅበሩ ያደረገውንና ያለበትን ውጣ ውረድ ሲያወያየን ዋለ። በማግሥቱ የምረጫ ቀን ሰለነበር እንደልማዳችው ጽሕፈት ቤቱ የራሳችውን አስመራጭ ኩሚቴ መርጠው ለቤቱ አቀረቡ። ወዲያወኑ የስብሰባው ተካፋዮች የጽሕፈት ቤቱን አሠራር በመቃወም አስመራጭ ኮሚቴ ከቤቱ ውስጥ መመረጥ እንደአለባቸው አሳሰበ። አመራሩ ግን ፍንከችም አላለም። በዚህ ጊዜ ነበር የቤቱ መንፈስ ቅይርይር ያለው። በአዳራሹ ውስጥ ተወካይ መስለው ነጭ ለባሾች ተኩልኩለው ነበር። ከመካከላችን አንዱ እንዲህ አለ “የዝምብ መንጋ ወስከምብያ አይከፍትም” ሲል ተሰብሳቢው አጨበጨበ ነገር ግን ከተነሸ ዲቃዎች በኋላ እሱ ያለው አባባል ሳይሰካ ቀረና ብዙ ከተጨቃጭቅን በለስ ቀንቷቸው ሻጥረኞቹ አዳራሹን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉት። የስብሰባው አቅጣጫ ደስ ያላለው ፍሥሓ ጽዮን ተኬኤ ቢሮ ሄዶ ስልክ በመደውል ግማሽ ስዓት ባልሞላ ውስጥ መንግሥትን ወክለው ዶክተር ሥዩም ተሸሞው መጡና ቤቱን በሊቀ መንበርነት ኣንዲመሩ ተደረገ (ዶክተር ተብየው ዩኒቨረሰቲ የሲቪክ መምህር ነበሩ)። እሳችውም መንግሥት ቀደም ብሎ አዘጋጅቷቸው ስለነበር መምረጥ ያለባችው እነ ማን እንደሆኑ ቀደም ብለው ሰለሚያወቁ አሁንም እነ ፍሥሓ ጽዮንና ቡደኖቻቸው ያለ ምንም ተቃውሞ አስመረጡ። ለዚህም ሥራችው ጃንሆይ መልካም ፈቃዳችው ሆኑ የጎንደር ከተማ ከንቲባ አድረገው ሾሟቸው። ትግሉ ግን አንዴ ሲዳፈን አንዴም ሲጋጋል ቀጥሏል።

የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም አብዮት በፈነዳበት ወቅት ኢሠአማ ከየጠቅላይ ግዛቶቹ ማለት የማኅበሩ አባለት የነበሩ ሁሉ ወኪሎቻቸውን በመላክ ጠቅላላ ስብሰባ ከየካቲት ፳፫ ቀን አስከ ፳፮ አድርገን ፤ ከማግሥቱ ጀምረን አገር አቀፍ የሥራ ማቆም ጀመርን። ትልቅ ሰህተት ያደረገነው መሪዎቻችን እነ ፍሥሓ ጽዮንና ጓዶኞቹ ብቻ እንዲሁኑና ከሠራተኛው ወኪሎቻችን መካከል የኛ ደጋፊዎች የሆኑ አንድም ሰው ባለመጨመራችን ጥረታችን ባጭር እንዲቀጭ ተደርጓልል። ማቆሙን ሐሙስ ማለት የከቲት ፳፰ ቀን ጀምረን ጥያቄወቻችን ሳይመለሱ ከሰኞ ጀመሮ በሻጥረኛው ፍሥሓ ጽዮን መሠሪነት ከስብሰባው ወጣ በማለት ለኢትዮጵያ ሬደዮና ተሌቪዝን ሠራተኛው ተስማመቷልና ሁሉም ወደ ሥራው እንዲመለስ ሲል ቀጭነ ትዕዛዝ አሰተላለፈ።  ሠራተኛው ከወኪሎቹ ሳይሰማ ሰኞ መጋቢት ፪  ቀን ወደ ሥራው ተመለሰ። ማኅበራቸውን ወክለው የመጡት ሁሉ አብዛ ኛዎቹ በሌላ ቀን ተሰብሰበው ከወስላታው መሪዎች ጋር የነበረውን ግኑኝነት አቋረጡ። በግለጽና በኅቡዕ ሥራውን ጀመረ።

በዚህም ውለታው ባጭር የተቀጨው የልጅ መኮንን እንዳአልካቸው መንግሥት የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ኮሚሽን በተቋቋመት ጊዜ አብሮ ሠራተኛውን ወክሎ እንዲሠራ ተደረገ። ይኽ ዓይነት ንቀት የበለጠውን ቁጣችንን ስለ አባባሰው ሁሉንም መሪዎች ተብዮች አሽቀንጥረን ለመጣል ትግሉን አባባስነው ፣ አጧጧፍነው። ከዚያማ ማን ያቁመን!!!!

ወደ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ስንመጣ ደግሞ መስከረም ፲፫ ቀን ኢሠአማ አገር አቀፍ የሥራ ማቆም እያደረገ እያለ ዓለም አብዲና ጓደኞቹ ከደርግ ጋር በምስጢር ተነጋግረው ስለነበር በተለይ ከህንድ ጨርቃጨርቅ መሪዎች በተልይም ደግሞ ጣዕም የለው እሸቴንና ሌሎቹ መሰሎቹን በመያዝ እነሱን ለሚቃወሟቸው ሳይነገሩ  እንዲ ከሽፍ አድረጓል። ዋናው ዓለማቸው ግን የሥም ዝርዝርና የድርጅታችውን መሪዎች ሥም ለደረግ በመስጠት ለማሳሰር ነበር። ምኞታችው ግን ሳይሳካ ቀረቷል። በዚህ ሻጥር አሠራር ግን ፍሥሓ ጽዮንና በየነ ሰሎሞን አልተሳተፉም። ቀኑን ባለስታወስም ቅሉ መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ደርግ አስሯቸው ነበርና እነማርቆስ ሐጎስ ሲፈቱ ማለት  በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም  አብረው ተፈተዋል። ይኽ የሥራ ማቆም አድማ ዓለም አብዲና ጓደኞቹ ካሰናከሉት ቀን ጀምሮ የማኅበሩን ጽ/ቤት በሠራተኛው ቁጥጥር እንዲሆን ለማደረግ የተጠነሰሰበት ወቅት ነበር። ከግምባር ቀደም ተሳታፊዎችና አሰተባበሪዎች አንዱ ማርቆስ ሐጎስ ነበር። ዓለማችን ከግብ ለማድረስ በኢሠአማ አደራሽና በሌላ ማኅበራት አዳረሾች እየተሰበሰብን ትግሉን አካሂደናል።

ደርግ ዓለም አቀፉ የመጀመሪያውን የግንቦት ቀን (May Day 1975) ለማክበር ከምሥራቅ አውሮፓ አገሮች መሪዎችና የማኅበር ተወካዮችን ጋብዞ ነበር። ይህን ከሥራ ላይ ለማዋል ሰርቶ አደሩ እንዲተባበሩት በዓለም አብዲ በኩል ጥሪ ተደርጎ ነበር። የደረግ ጥሪ እንደተሰማ ሚያዝያ ፲፰ ቀን ቅዳሜ ኢሠአማ አደራሽ በመስብሰብ ማለት ማድረግና አለማደረግ ያለብንን ተናጋግረን ነበር። ዓለም አብዲ የኛን መስብሰብ በቅድሚያ ስለሚያውቅ ለሥራ ቢሮ ገብቶ ነበር።  እሱም ብቻ አይደለም የሱም ደጋፊዎቹ መካከላችን ነበሩ። ስበስቡ ከተነጋገረባቸወ አጀንዳዎች መካከል ዓለም አብዲን ማገት ነበርና አዳረሹ ውሰጥ ትንሽ መጋዘን አሰገባነው። ደርግም ወዳጀነቱን ከሱ ጋር በማድረግ ሠረቶ አደሩን ማሰቀየም ቀጠለበት ፤ ወዳጁ ደርግ ዓለም መታገቱን ያዩ ወዳጆቹ ሰለ ደወሉላቸው በፍጥነት በምጣት ከነበረበት ጠባብ የዕቃ ቤት ወደ ትልቁ ቢሮው ወሰዱት። የሠራተኛው ወኪሎች ፍልጎታቸው አንድና አንደ ብቻ ነበር። ለብዙ ዘመናት በጉለበትና በሻጥር የያዙትን ሥልጣን ለግምባር ቀደሙ መሪዎች እንዲያሰረክብ እንጂ ማናቸውም ቢሆን እንዲታሰሩ ፍላጎቱም አጀንዳውም አልነበርንም። አሁንም የሠራተኛው ተወካዮች የሠራተኛውን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲከበር ከፈለገ ተናጋሪዎቹና አስተባባሪዎቹ ከኛ መካከል (ከሠራተኛው መሪዎች መካከል) ካልሆነ በስተቀር በምንም ዓይነት ተሳታፊ እንደማንሆን ለወኪላችው በግልጽና በማያወላውል ሁኔታ እምብኝ አሻፈረኝ አልናችው። ደርግ ከመጨነቁ የተነሳ ከመዋረድ ብሎ ወኪሎችን ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ደሜ(ደምሴ) ዴራሳንና ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) እንዳለ ተሰማን ኢሠአማ ጽ/ቤት ድረስ ሚያዝያ ፳፩ ቀን በመምጣት ስብሰቡን  አነጋግረዋል። ከብዙ ውይይትና ንትረክ በኋላ ወኪሎቹ ጉዳያችሁንና ብሶታችሁን ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላ እንፈተዋለን አሁን ግን የሠርቶ አደሩን ቀን በጋራ እናክበር ሲሉ ቃል ገቡልን ፤ እኛም ተሰማምተን በቀጠሩን ቀን ግንቦት ፱ ደረግ ጽ/ቤት እንገኛለን ስላሉን ተስማምተን ተለያየን።

በማልሥቱ በዓሉን በዓለም አብዲ ተናጋሪነት በጋለ ስሜት አከበረነው። የቀጠሮው ቀን ደርሶ በማርቆስ መሪነት ወደ ደርግ ቢሮ አመራን። ትንሽ ደቂቃዎች ከቆዩን በኃላ ዘበኛው የቀጠሯችሁ የደረግ አባለት በሥራ ምክንያት ከከተማ ውጭ ስለሄዱ ማነጋገር አትችሉም ሲሉ ገና በር ላይ መለሱን። እኛም በመጣንበት መንገድ ተመልሰን ወደ ኢሠአማ ጽ/ቤት አመራን። አንድ የማኅበር መሪ በአዳራሹ ስብሰባ ሲካሂድ ስለነበር እዚያው ውሰጥ ባለቸው ቡና ቤት ተሰባሰበን በጥልቅ ከተወያንበት በኋላ ቤቱ ጽ/ቤቱን በቁጥጥር ሥር እንዲያደርግ በአንድ ደመፅ ተስማማ። ቅዳሜ ግንቦት ፱ ቀን ጀምረን እስከ ሰኞ በሦስት መደብ በመከፋፈል ጽ/ቤቱን መቆጣጠር ጀመርን። ሰኞ ደረሰና ወደ አሥራ አንድ ስዓት ገደማ ደረግ በኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ተካ ትሉ የሚመራ ወታደር ልኮ አዳራሽን ከበብው። ፉአኔው ሻለቃ አሁኑኑ አዳራሹን ለቃችሁ ካልወጣችሁ ባለችሁበት እንጨርሳችኃለን እያሉ በተደጋገጋሚ ሲያቧሩቁብን ማርቆስ ሐጎስ በሰከነ ልሣኑ አዳራሹን ለቀን እንድንወጣና ትግሉን ውጭ ሆነን መቀጠል እንደሚኖረብን ከገለጸልን በኋላ አንድ በአንድ አዳራሹን ትተን ወጣን። ደረግም በሁለት ስዓቱ ዜና በሬድዮና በተሌቪዠን ኢሠአማ ከዛሬ ቀን ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ተዘግቷል ሲል ሕዝቡን አስታወቀ።   በማግሥቱ በኅቡዕ በመደራጀት የኢሠማ ትንሣኤ ኮሚቴ በሚል ሥም ሥራችንን ቀጠልን። እንዲያውም ትግሉ ከምን ጊዜም የበለጠ እንዲጧጧፍ የደርግ እኩይነት በግለጽ የሠራተኛው ጠላት መሆኑን ለአባሎቻችን አረጋገጥልናቸው። ሆኖም ደርግ በየመሥሪያ ቤቱ እየዞረ ማኅበሩ የተዘጋበትን ምክንያት ገለጻ በሚያደርገበት ወቅት ብዙም ሰሚ ስላለገኝ ቅዳሜ ግንቦት ፳፫ ቀን የገንዘብና የመድኅን ድርጅቶች እንዲሁም አሠሪዎችና ሠራተኞች አንድ ላይ ፓርላማ በተላያዩ አዳራሾች በመሰብሰብ የደረጉ ተወካኦች ሻለቃ ሲሰይ ሀብቴና ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ብረሃኑ ባየህ ጽ/ቤቱ ከሰኞ ጀምሮ እንዲከፈት ወስነናል አሉን።። አያይዞም በማግሥቱ መሪዎቻችንን እኛው እራሳችን ከመካከላችን እንደንመረጥ ወኪሎች ከየማኅበሩ ተሰባስብን በኢሣአማ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን ሊቀ መንበርና ዋና ጸሐፊ ማርቆስ ሐጎስንና ተሰማ ደሬሳን መርጠናል። እኛም ባደረግነው ድልና ውጤታማ ሥራችን በደስታ መረቀነን በመጣንበት ማንገድ ወደ ቤቶቻችን አመራን።

ማርቆስ ሐጎስ ከደርግም በፊት ማለትም በጃንሆይ ዘመን እንዲሁም ኋላም የጸጥታው ክፍል ይከታተለው ነበር። እንዳጋጣሚ ሆኖ ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ አግኝቸው የማላውቀው የልጅነት ጓደኛዬ ጸጥታ ክፍል የሚሠራ ሰለ ማርቆስ ሐጎስ ትውልድ ይጠይቀኛል። ለምን እንደጠየቀኝ ገብቶኛል። ብዙ ጊዜ በፊትም አሁንም የአባቱ ሥም «ሐጎስ» የሆነ ከጀብሃና ከሻብያ ጋር ያገናኙት ነበርና ይህ ሥም በትግርኛ ተናጋሪው ሕዝባችን የተወደደ የሥም መጠሪያ ነው ነግር ግን በሥሙ ብቻ የታችኛው ወይም የላይኛው ትግራይ ይሁን ግን በቀላሉ ለማወቅ አንድ ሰው ሊያውቅ አይችልም ካልተቀራረብክና ግለ ሰቦቹን ካለወክ በስተቀር። ይህ የልጅነት ጓደዬ በተወለድነበት አካባቢና ትምህርት ቤቶች ከሐጎሶች ጋር አብረን እንደተማረነ ሳስታወሰው ተገረመና አይ! እውነትክን እኮ ነው እንዲያው ዝም ብሎ መለደፍማ አይቻልም ተባባልንና እንዳንተውና እንደኔው ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሠርቶ አደሩ ጠበቃ መሆኑን አስረግጨለት ተለያየን። ለኔ ወንደሜ ነው ብዙ ቁም ነገሮችን አስተምሮኛልና ከኢንግዲህ ወዲህ በአንተ በኩል አትከታተለው ለሌሎቹም ከአንተ ጋር የሚሰሩ ባልደረቦችህንም ነገራቸው ተባብልን በመቀላለድ በሠላም ተለያየን። እሱም ብዙ ሳይቆይ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም መጨረሻ ላይ ደረግ ጡረታ አስወጣው።

ማርቆስና ጓደኞቹ ትግሉን ቀጠልን። በእሱም መሪነት መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አገር አቀፍ የሥራ ማቆም ተጠራና አሁንም ፋሽስቱ ደረግ የስዓት እላፊ አዋጅ አወጀና ተቃውሞው ከሸፈ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ብዙዎቹ የማኅበር መሪወች በሚሠሩበት መሥሪያ ቤት እየያዙ ከሦስት ወር አስከ ሰባት ወር ድረስ አስሯቸዋል። በግምባር ቀደም ከታሰሩት መሪዎች መካከል አንዱ ማርቆስ ሐጎስ ነበር። የታሰረበትም ቦታ ሌሎቹን ጨምሮ ማይጨው ሠፈር ጃን ሜዳ ከመድረሳችን በፊት በክቡር ዘባኛ ግቢ ውስጥ ነበር። እኔ እንደማስታወስው አሱና ሌሎቹ መሪዎች የተፈቱበት ቀን ዓርብ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ነበርና እንዳጋጣሚ ተገኝቼ ሁሉንም ተቀብያቸኋለሁ። ማርቆስና እኔ ግን በፋሽስቱ አስከ ተገደለብት ቀን ጀምሮ አልተያየንም። እኔም አሱም በተሰጠን የሠራ ክፍልፍል ምክንያት አብረን እንደንሠራ አልተደረገም በዚያም ምክንያት ተገናኝተን አናውቅም ነበር። መስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ደርግን ለማበረከክ ለሦስተኛ ጊዜ የሥራ ማቆም ሙከራ አደረገን ነበር። በማግሥቱ ኮሎኔል መንግሥቱ (ያኔ ሻለቃ) ላይ የተደረገው የመግደል ሙከራ ክፉኛ ከሸፈ። ነገሮች ሁሉ ተለዋወጡ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነበር ፎቶዎቻችን በየቦታው እንዲለጠፉ በሌ/ከሎኔል አጥናፉ አባተ ፊርማ ጥብቅ ምሥጢር በሚል በድፍን ኢትዮጵያ እንዲሰራጭ የተደረገው።

ከሠላሳ አራት ዓመት በኃላ የሚከተለውን ታሪኩን ሳነበውና ሥዕሉን ሳየው ብዙ ትዝታዎች ቀሰቀሱበኝና እኔም የካቲት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም አብዮት ትዝታ በአዕምሮዬ መጠብኛና የማስታወሰውን ያህል ባጭሩ ለወዲፊት የሠራተኛው መሪ ልምተሆኑ ወይም የታሪክ ተማሪዎች ሊረዳ ይችላል በማለት ባጭሩ የማውቀውን ያህል አቅርቢያሁ። ብዙ ጓዶኞቹ በይሕወት ያላችሁት ደግሞ በተጨማሪ የምታውቁትን ጨምርመር አድርጋችሁ እንድትዘክሩት በማክበር አሳስባለሁ። አበራ ገሙን የመጀመሪያው የማኅበር መሪ ሁሉም ላብ አደሮች ጫማ ካለደረጉ እኔ አላደረግም ብሎ አስኪሞት ድረስ በባዶ እግሩ ይሄድ የነበር ጥሩና አሰተዋይ መሪ ነበር። እሱንም እንዘከረው። በተጨማሪም ማርቆስ ሐጎስ ከመምህራን መሬዎች ጋር ማለት ከዮሐንስ ብርሃኔና ከብርሃኑ እጅጉ(ሁለቱም እንደሱ ተሰውተዋል) ፤ እንዲሁም ከሌሎቹ ጋር ሠረቶ አደሩን ወክሎ የሠራ ጀግና ኢትየጵያዊ አርበኛ ነበር።

## ማርቆስ ሐጎስ «የሠራተኛው ሠማዕት»
## ከአደራ መጽሔት የተወሰደ

አምባገንን ገዣዎች ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ለሕዝብና ለሕግ የበላይነት የሚታገሉና የሚያታግሉ ግለሰቦች ሁሉ ባላቸው አቅምና ልዩ ልዩ ስልቶች አሰቃይተውና አሳድደው በመግደል ከገጸ ምድር ሲያጠፏቸው ኖረዋል። አምባገነኖች ሁሉ አንድ እስከ መጨረሻው ያልተሳካለችው ነገር ቢኖር የሕዝብን የነፃነት ትግል ስንከለው ለማስቀረት ያለመቻላቸው ነው። የየትግሉ መነሻ ምክንያት ዓይነትና ደረጃ ቢለይም እያንዳንድ ትውልድ የየራሱ ጀግኖች ሠማዕታት አሉተ። ይኖሩታልም።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውሰጥ የሕዝባዊ ገድል ታሪካቸው ያሳለፉት መከራና ስቃይ ተመርምሮ ያልተጻፈ የከፈሉት መሪር መሥዋዕትነት ያልተዘከረ እጅግ ብዙ የሕዝብ ወገን ባለታሪኮች አሉ።

አምባገነን ገዥዎችና ሐሳዊያን የታሪክ ጸሐፊዎች እውነቱን ሁሉ የሐስት ጥላሸት እየቀቡ ቢያደበሰቡስትም የዘመነ ሐቅ ፀሐይ ስትወጣ የጻፉት ነገር ሀሰት ሁሉ እንደ ትብያ በንኖ እውነተኛው ታሪክ እንደ በጋ ሌሊት ከዋክብት ይንተገተጋል። ለዚህም ነው ከዛሬ ፴፪ ዓመታት በፊት የፋሽስታዊ ደርግን ኢፍትሐዊ አገዛዝ በቆራጥነት ሲታገሉ ከነበሩት የኢትዮጵያ ሠራተኞች መካከል የኢሠአማ ፕሬዚዳንት የነበረው የማርቆስ ሐጎስ ትግልና የሠማዕታት ታሪክ በአምባገነኖች መቃብር ላይ እንደ ጸደይ አባባ ፈክቶ እንደ በጋ ንጋት ፀሐይ ደምቆ የበራው።

የ፲፱፻፷፱ ዓ.ም መጋቢት ወር ሁለተኛው ሳምንት እንደተጠናቀቀ ፒያሳ ከግሪክ ኦርትኦዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደቡብ ከፍታው ቦታ ላይ ባለ የቀድሞ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከበተረ ደጀኔ ጋር ሳገኘው  ግርማ ሞገሱ ምንኛ ደስ ይል እንደ ነበር ዛሬም ድረስ ይታየኛል። በተገኘበት እንዲያዝ ወይም እንዲገደል የተወሰነበት ፎቶግራፉ በየመሥሪያ ቤቱና በየአደባባዩ የተለጠፈበት ስው በጎቡዕ መኻል ፒያሳ መኘኘቱ ያስገርም ይሆናል። **ቀደም ሲል ታስሮ በነበረበት ወቅት ጀርባና ትክሻው ላይ በደረቅ አኮረማጀና ገላ በሚተለትል አለንጋ ተገርፎ በማንዘሪያ ኤሌክትሪክ ተጠብሶ ሰምበሩ እንደ ገመድ ተጋድሞ የሚታየው ቆዳው እጅግ ስላመመው ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ በጎቡዕ መምጣቱን በትረ አጫወተኝ።** እኔ ሳገኘው ከሕመሙ ድኖ በደህና ሁኔታ ላይ ነበር። በሠራተኛው ማኀበራት ትግል ላይ በስፋት ሰለ ምንተዋወቅና በሌላኛው ትግል መስመርም ስለ ምንገናኝ ሠፊ የመግባቢያ ቋንቋ  ነበረን። በውቅቱ እኔም ሥራ ለቅቄ በመንከራተት ላይ ሰለ ነበርኩ የማርቆስን የሞት መርዶ በሬድዮ የሰማሁት ጎጃም ቨረንዳ አንዲት አልባሌ ሻሂ ቤት ውስጥ ነበር። ዛሬ ከ፴፪ ዓመታት በኋላ ወደዚያ የሠራተኛ መብት ታጋይ ጀግና ቤት ሄጄ የሕይወት ታሪኩና የጀግና አወዳደቁን ከባለቤቱ ከወይዘሮ አልማዝ ገብሩ ጋር እያወራሁ በእገረ ሐሊና ወደነዚያ የመከራ ጊዚያት ነጎደኩ። ከመሪር ትዝታዎቼ መለስ ስለ ባለቤታችው የሚከተለውን ሐቅ አወጉኝ።

በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም የኢትዮጵያ የምድር ባበቡር ሠራተኞች ማኅበር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራትና እውነተኛ መሪዎቻቸው ለላብ አደሩ መብትና የሥራ ነፃነት እጅግ ከፍ ያለ ትግል አካሂደዋል። እውቅ የላብ አደሩ መሪዎችም በሚመር ስቃይ ውስጥ የዘለቀ የሕይወት መሥዋዕትነት ከፍለዋል።

ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የኢሠአማ ጠቅላላ ጉባኤ ያስተላለፈው ውሳኔ (ገፅ፩) «የኢትዮጵያ ሠራተኞች ትግል ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ያልተጻፉ ያልታወቁና የተደበቁ ገድሎች አሉት» ይላል። ፋሽስታዊ ደረግን እየታገሉ በክብር ከወደቁት ሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች አንዱ የነበረው የኢሠአማ ፕሬዚዳንት የአቶ ማርቆስ ሐጎስ የመሥዋዕትነት ገድል እነሆ!

«አቶ ማርቆስ ሐጎስ በቀድሞው የከፋ ክፍለ ሀገር በየም አውራጃ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ተወለደ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ወሊሶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አዲስ አበባ ጄኔራል ዊንጌት አዳሪ ት/ቤት ተማረ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ባጠናቀቀበት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የአስተዳደር ሥራ ሥልጠና ሰጥቶና አወዳድሮ ሠራተኛ መቅጠር ይፈልግ ሰለነበር ማርቆስ ተወዳድሮ አለፈ። በሥልጠናው ወቅት ባሳየው ችሎታ

ከተመረጡት አንዱ ሆነና እዚያው ተቀጠረ» አሉ ወይዘሮ አልማዝ ሚች ባለቤታቸው በዓይነ ሕሊና እይታቸው።

«ከዚያም ለተወሰኑ ዓመታተ አገር ግዛት ሚኒስቴርና (አገር አስተዳደር) አጠር ላለ ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠረቷል። ለምን እንደተመለሰ ባላውቅም እንደገና ወደ ማዘጋጃ ቤት ተመልሶ ነበር። ዳግመኛ ማዘጋጃ ቤትን ለቅቆ ኢምፔሪያል ኢንሹራንስ እንደ ተቀጠረ ተጋባን። ከዚያም ይኸኛውን ለቅቆ ፓን አፍሪካን ኢንሹራንስ ገባ። ኢንሹራንስ ይሠራ በነበረበት ጊዜ ነበር ወደ ሠራተኛ ማኅበር የተቀላቀለው። እዚያ ከገባ በኃላ ዕረፍት ብሎ ነገር አልነበረውም። በተለይም የኢሠአማ ፕሬዚዳንት ከሆነ ጀምሮ ሠራ እየበዛበት ሄደ። የሠራተኛው የመብት ጥያቄና ትግል እየተጠናከረ በመምጣቱ መስከረም ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የሥራ ማቆም አድማ ተካሄደ። ያን አድማ ካቀናበሩትና ከመሩት ቀንደኛው አንተነህ ተብሎ ታሰረ። ከሰባት ወራት በኋላ በዓለም ሠራተኞች ድርጅት(ILO) ግፊትና በሠራተኞች የትግል ጫና ተፈታ በእስር ላይ እጅግ ከፍተኛ ስቃይና መከራ ደርሶበታል። ልክ በዓመቱ መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም አንድ ሌላ ከባድ ሙከራ መጣ። በተገኘበት እንዲገደል የሚል ትዕዛዝ በመንግሥት በኩል ተስጦቶ ስለነበር ኑሮና እንቅስቃሴው ሁሉ በጣም አስቸጋሪና በድብቅ ነበር። የት ውሎ የት እንደሚያድር አናውቅም ነበር» አሉና አንድ አሳዛኝ ትዝታ ፊታቸው ላይ አጠላ። ከእፍታ ዝምታ በኋላ «ከአዲስ አበባ ለመውጣት እንዲያመቸው አስቦ ይመስለኛል ወደ እንጦጦ ኪዳነ ምህረት በሚያስኬደው መንግድ ዳርቻ ላይ ወደሚገኘው ወደ ወላጆቹ ቤት (አባትና እናቴ) ይሁዳል። ወሎ እንኳ አላደረም። ምሽት ላይ ወጥቶ ለመሄድ በመነሳት ላይ ሳለ ምግብ በልተህ ትሄደላህ ብለው ለጥቂተ ጊዜ ያቆዮታል።

ማን እንደጠቆመበት አይታወቅም ለካስ የደርግ ወታደሮች ተከታትለውት ኖሯል። ቤታችን ከበው የአጥሩን በር ያንኳኳሉ። በጣም መሸቷል። ቤታችን መከበቡን እንደተረዳ ወደ ልዩ ልዩ ቦታዎች ሲዘዋወር የሚጠቀምባቸው መታወቂያዎችና ሌሎች በእጁ የነበሩ መረጃዎች ወደ ደርግ እጅ እንዳይገቡ የውሀ እንስራ ውስጥ ከተታቸው። የተለያዩ መታወቂያዎች የያዘው በወቅቱ በብዙዎቹ ዘንድ በመልክ ወይም በሥሙ ይታወቅ ስለ ነበር ሥሙን ለመቀያር ታስቦ የተደረገ ይመስለኛል።» አሉ ፊት ለፊት የነበረውን የማርቆስን ፎቶ በኩራት እየተመለከቱ «ምን ጊዜም በትግል ላይ ያጋጠመውን ችግርና መከራ ለሌሎች አሳልፎ የማይሰጠው ማርቆስ እቤት የነበሩ ሕፃናት በጓሮ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ የከበቡትን ወታደሮች ሊጋፈጥ ተዘጋጀ። አባቴ እኔ በሩን ልከፈት ቢሉት አይሆንም የምከፍተው እኔ ነኝ አላቸው። በዚህ መኻል ፈንጠር ብለው ቤቱን የከበቡትን ወታደሮች አንድ ጥይት ተኮሱ። እሱም በምላሹ አንድ ተኮሰ። ከበው የነበሩት ወታደሮች እቤት ውስጥ ያደፈጠ ተጨማሪ ኃይል ይኖራል ብለው የጠረጠሩ ይመስለኛል ቦታ ለመያዝ አፈገፈጉ። ጨለማ በመሆኑ አነርሱ ሲያፈገፍጉለት እርሱ ሽጉጡን አቀባብሎ ሲጠባበቅ በተከታታይ ተኮሱበት፤ አሱም ወደ እነሱ መተኮሱን ቀጠለ። በመጨረሻ ሁለት ጥይት ብቻ ሲቀረው ተኩሱን አቆመ። ወደ አስፋአልት ወጥቶ የድርጅቱን የትግል መዝሙር ዘምሮ መፈክሮችን አሰማ። በመጨረሻም እጄን ለደርግ አልሰጥም ይል ስለ ነበር አንገቱ ላይ ከማንቁርቱ ከፍ ብሎ በቀኝ የመንጋጋው ሥር ወደ ላይ ተኩሶ በአንዲት ጥይት ራሱን አጠፋ እንጂ ደርጎች አነጣጥረው አልመቱትም፤ ደርግ የእኔ ወታደሮች ናቸው ተኩሰው የመቱት ብሎ ያስነገረው ፍጹም ሀሰት ነው። ደርግ በተደጋጋሚ በሌሎች ላይ ሲዋሽ እሰማ ነበር። ይኸውም ስለ ማርቆስ አሟሟት ባስነገረው ዜና ላይ እርሱ ያልሠራበትን መ/ቤት እንደ ሠራበት መግለጹና ያለፈጸመውን ድርጊት አድረጓል ማለት

ነበር» ብለው መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም የወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከፊል የመጀመሪያ ገጽ ሰጡን። አነበብነው። (እኔ የትግል ጓደኛው ማስታወሰው ግን ማርቆስ እራሱን የገደለው ዓርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥበያ መጋቢት ፲፯ ቀን እንደ ነበር ነው።) «አዲስ አበባን ከአድኃሪያንና ከቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ለማጽዳት በተደረገ አብዮታዊ ምንጠራ በከፍተኛ ፲፮ ቀበሌ ፬ ውስጥ ትናንት ምሽት የቀድሞው የኢሥአማ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው ማርቆስ ሐጎስ በአሳሽ ጓዶች ተገድሏል። ማርቆስ ሐጎስ በመኖሪያ ቤቱ ተደበቆ እጅ አልሰጥም ከማለቱም ሌላ ለፍተሻ በተሰማሩት አሳሽ ጓዶች ላይ ተኮስ በመከፈቱ በተደረገው የተኮስ ልውውጥ ሊገደል መቻሉ ተገልጧል። …» ይላል። ቀሪውን አርቲቡርቲ ትተነዋል።

«ሬሳው አስፍልቱ ላይ ወደቀ። ወታደሮቹ *ቢአር* ጠምደው በመጡበት ጂፕ ላይ አስከሬኑን ጭነው ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ወሰዱት። የ፷ ዓመት ሽማግሌ የነበሩትን አባቴን አቶ ገብሩ አረጋይ ሣህሉንም ወስደው ጃንሜዳ ክቡር ዘበኛ መምሪያ ለሦስት ወር ያህል አሰሯቸው። እናቴን ባይወስዷትም ቅሉ በጣም አንገላቷት። ለአባቴ ስንቅ እንኳ እንዳናቀበል በወቅቱ የት ቦታ እንዳሰሯቸው አናውቅም ነበር። የማርቆስ የክርስትና አባት ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ይሠሩ ስለ ነበር አስከሬኑን አይተውታል። ሬሳውን እንዲሰጡን ጠይቀን ነበር ነገር ግን አስፈራርተው አባረሩን። ልቅሶና ሐዘን መቀመጥ ፣ ሐዘንተኛውን ማጽናናት በተከለከለበት በዚያ የመከራ ዘመን አስከሬን የጠየቅነው እንዲያው ምናልባት እንሞክር በማለት እንጂ ደርግ ይራራል ብለንስ አልነበረም። ቁርጡን ማወቅ ግን ጥሩ ነበር። የት እንደተቀበረ ተከታትለው የነገሩን የክርስትና አባቱ ነበሩ። የተቀበረው ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ጀርባ ደን ውስጥ ነበር። እዚያ መቃብር ቦታ ለሕሊና በሚከብድና እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በደርግ የተገደሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ባንድ በጅምላ መቃብር ውስጥ አምስት ፣ ስድስት ፣ አሥርና ከዚያም በላይ ተደራርበው እንደተቀበሩ መቃብር እየተከፈተ አጽም በተለቀመበት ጊዜ እዚያው ተገኝቼ አይቻለሁ።

ማርቆስ በሞተበት ዕለት የለበሰው እኔ እራሴ በጄ የሠራሁትን ግረይ ሹራብ ነበር፤፡ መቃብሮቹ እየተቆፈሩ ተራ በተራ ሲከፈቱ የማርቆስን አጽም ለብሷት የነበረውን ሹራብ ለማወቅ እንደምችል ሙሉ እምነት ነበረኝ። እውነትም ያቺ ለብሷት የነበረችው ሹራብ አጽሙን ይዛ ተገኘች። እንዴት ደስ እንዳለኝ መግለጽ ያቀተኛል። በዚያን ጊዜ ወጣቶችና ሌሎቹም በቀይ ሽብር የተገደሉ ስለ ነበር ማርቆስ የተቀበረው ከነሱ ጋር ነው። በቀይ ሽብር የተገደሉ ወጣቶች የተቀበሩትም እዚያው ነበር። የብዙ ወጣቶች ሬሳ ከመቃብር በጅብ እየወጣ ተበልቷል። በዚህም ምክንያት ሲሞቱ በለበሱት ልብስ ምልክት እንደተገኙት ሊገኙ ያልቻሉት መዓት ናቸው።

የማርቆስ አጽም ለይተን ካወቅን በኋላ አጥንቱ ተለቅሞ በአዲስ አንሶላ ተጠቀለለ ፣ ከዚያም ከሌሎቹ መሰሎቹ ጋር በመኪና ተወሰደ። ይህ ሁሉ ሲሆን አንዱ ልጄ አብሮኝ ነበር። አቶ ማርቆስ ስንት ልጆች አሉት? አልናቸው ሐሳባቸውን ከመካነ መቃብር ወደ መካነ ሕይወት ለመመለስ። “አምስት ልጆች አሉን ፣ እነሱም ታደሰ ፣ ዳዊት ፣ አምሳሉ ፣ (ሴት) ዘመነና ደጉ ይባላሉ። የመጨረሻው ልጃችን አባቱ ሲሞት የአንድ ዓመት ሕፃን ነበር። ዳዊት ግን ሞቷል ሠራተኛ ነበር። አንዲት ልጅ አለው ፣ እሱን እያሳደኩ ነው ። ሁሉም ራሳቸውን ችለዋል ፣ ለቁም ነገር በቅተዋል። በአሁኑ ጊዜ ከኔ ጋር

አብሮ የሚኖር የለም። ሁሉም በትምህርት ፣ በሥራና በኑሮ የተሳካለቸው ፣ በመልካም ሥነ ምግባር ያደጉ ፣ የተባረኩ ጥሩ ዜጎች ናቸው። ሳሳድጋቸው አላሰቸገሩኝም።

ስለ አባታቸው የማያውቁት ነገር የለም። ዘርዝሬ ነግሬአቸዋለሁ። በአንድ ወቀቅት ትልቁን ልጅ የኢሕአፓ ወረቀት በትነሃል ብለው ያዙት። እሱን ሲይዙ እኔ ከሥራ ወደ ቤት በመግባት ላይ ሰለ ነበርኩ ልቀቁልኝ በዬ በመጠየቄ ደበደቡኝ። ደግነቱ ገረፈው በማግሥቱ ለቀቁት።» ብለው በድጋሚው የግፍ ጥቃት ፊታቸው ቅጭም አለ። በመራራው ትዝታ ምክንያት ላፍታ ያህል ዝም አለንና ፣
«እስቲ ስለ ቤተሰባዊ ግኑኝነት ይነገሩን» አልናቸው። ይዟቸው ከነጎደው ሐሳብ መለስ አሉና ግርማ ሞገስ የተላበስ ደርባባ ፈገግታ እያሳዩ «ሠራተኛ ማኅበር ውስጥ ከገባ ጀምሮ ልጆቹን ለማየትና ለማጫወት ጊዜ አልነበረውም፤፡ የልጆችህን ሕይወት ተመልከት ፤ ተከታተላቸው ስለው የስንቱ ድሀ ልጅ እየተንገላታ ያድጋል ፤ ይማራል ፤ እናትና አባታቸው እየሞቱባቸውም ይኖራሉ። የስንቱን ሠራተኛ ሕይወት መከራ ውስጥ ገብቷል። ልጆቻቸው እየተራቡና የሚለብሱት እያጡ በሚንገላቱበት በአሁኑ ጊዜ እኔ ለራሴ ለልጆቼ የሠራተኛው ትግል በፍጹም አልነጠለነም ፤ የእኔ ልጆች ከማን ይበልጣሉ ፤ አንቺ ልጆቹን ተከታተይ ፤ አሳድጊ ፤ ምንም ወሰዋ አትግቢ ፤ እኔ እንደገባሁበት እወጣዋለሁ ይለኝ ነበር። እኔም አንዲት ፍሬ ሥራ ነበረችኝ። እሱ ከሞተ ልጆቻችንን ማን ያሳድግልናል? እንዴት ሆነው ያድጋሉ? እያልኩ ወደፊት ሰለሚሆነው ሁሉ እጨነቅና እሰጋ ነበር። እሱ ግን ቁርጡን ነግሮኛል። እግዚአብሔር ይመስገን አደጉ» አሉ ልበ ሙሉነት ባልተበገረ የእናትነት ወኔ። «እጅግ የሚያሳዝነኝ ግን» አሉ ብስጭት ብለው አንድ ፍትሕና ርትዕ ያጡበትን የመብት ጉዳይ በከፍተኛ ምሬት እያስታወሱ « ምናልባት ጡረታውን ይሰጡኝ እንደሆን ብዬ ጠየኩ ለካስ በየመ/ቤቱ የነበረውን ፋይሉን የደረግ የለወጥ ሐዋርያት ይባሉ የነበሩትን የጊዜው ሹመኞች ልቅም አድርገው አጥፍተውታል። ምን መነሻ ይገኘ ልጀምር? የተሰጠችኝን አንዲት የአየር መንገድ ደብዳቤ ደግሞ የትም አታደረሰኝም። የሚሉት ቢያጡ አስመስክሪ አሉኝ። እኔስ ማንነኝና አላስመሰክርም ብዬ ተውኩት። የአገልግሎት ክፍያም ሆነ ጡረታ አላገኘሁም። እርሱ ከከፈለው መሠዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር ግን ምንም አይደል። ሌላው የማልዘነጋው ነገር ማርቆስ የሞተ ሌሊት ወታደሮችቹ የወላጆቼን ቤት ሲበረብሩ ያገኙትን ገንዘብና ሌላ ቀላል ጠቃሚ ንብረት ሙልጭ አድርገው ወሰዱት።

አንድ ቀን ቤት ስፈትሽ ሻንጣ ሙሉ ዴሞክራሲያ የሚል ወረቀት አግኝቼ እንጀራ ጋገርኩበት። ከተገኘብን ይገድሉናላ! እነዚህን የምታዩዋቸውን የብዙ ማኅበሮች ማኅተም ያለባቸውን ወረቀቶች ያን ጊዜ አግኝቻቸው ቢሆን ኖሮ አልምራቸውም ነበር። ምክንያቱም እሱ አምስት ልጆች ትቶ ሞቷል ፣ እኔ ከሞትኩባቸው ደግሞ ሜዳ ላይ ፈሰው መቅረታቸው አይደለም ወይ? ብዬ መታሰርም መሞትም አልፈልኩም። እሱ እንዳይሞተበኝ በዬ በተደጋጋሚ ተው በዬው ነበር። እሱ ግን ለሠራተኛው ነፃነት ስል እሞታለሁ ፣ እንዲያውም አንቺ ትንሽ ሥራ አለሽ ፣ ያላ አንዳች ገቢ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ የሠራተኛ ሚስቶች አሉ። የኛ ልጆች ከማን ይበልጣሉ ይለኝ ነበር። በዚህ ምክንያት ቅሬታ አድሮብኝ ሁለት ጊዜ ከቤት ወጥቼ ወላጆቼ ያአባታቸው እንዳይበቃ ደርግ ልጆቼን ለብሔራዊ ውትድርና እያሳደደ መከራይን አሳየኝ። እኔም የዋዛ አይደለሁም ዘመድና ወዳጅ ቤት ደብቄ እያሳደርኩ ልጆቼንና ወንድሜን አተረፍኩ።» እንዳሉ ድንገት ስሜታቸውን ልውጥ አለና «ውይ! ውይ!ውይ! ያ ዘመን በዚች አገር ላይ አይደገም» አሉ እየተንገፈገፉ።

አጽሙ ከመቃብር ሲወጣ ምን ተሰማዎት? አልናቸው። «የደርግን ውድቀት እመኘው ስለነበር አጽሙ ሲወጣ ዳግመኛ የተፈጠርኩ ነው የመሰለኝ። ለኔ ትንሣኤ ነው። ሰው ሁሉ ሲያለቅስ እኔ ዘለላ እምባ ይወረደኛል አንጂ በልቤ የነበረው ደስታ ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን ያልኩት።  እንደኔ መከራ የደረሰበት ሁሉ የዚያ አረመኔ መንግሥት ውድቀት በጣም ያስደስተዋል እላለሁ። ለምን ደስ አይለው? ይለዋል እንጂ» አሉና ለዓመታት ባልተንበረከከ ጠንካራ ቅስምና እንድ ንጋት ጎህ በሚያስደስት የእናትነት ፈገግታ።
«ብዙውን ጊዜ ሰው ከሞተ በኋላ  ያልሠራውን መልካም ነገር መጨማመር የተለመደ ነው። እኔ ግን እውነቴን ነው የምነግራችሁ። ማርቆስ ደግ ነበር። ሙሉ ደሞዙን ይዞ መጥቶ አያውቅም። ለተቸገሩ የሚሰጥ ሩህረህ ነበር። ስንቱን ለዘርዝረው። ቤተሰቦቼንም ረደቶ ያቋቋማቸው እሱ ነበር። ልጆቼን ያሳደግሁት ራሴን እረደቼና ታግዬ ነው። ማንም አልረዳኝም። በፊት ትምህርት ሚኒስቴር ፣ ዩኒቨርሰቲ ውሰጥ በጸሐፊነት ፣ ጡረታ ከወጣሁ በኃላ ደግሞ የግል ማተሚያ ቤት ሰባት ዓመት ሠርቻለሁ። ኑሮ ባሰቸገረኝ ቁጥር ወቀት በቆሎና ስንዴ ቀላቅዬ እያሰፈጨሁ ልጆቼን አብለቻለሁ። ከልጆቼ ውስጥ ማንም አላሰቸገረኝም። እኔም የማርቆስን አደራ በሚገባ ተወጥቻለሁ። ቤተሰቦቼ ልጆቹን ወስደን እናሰድግ አንቺ ገና ልጅ ነሺ አግብተሽ መኖር ተችያለሽ ብለውኝ ነበር። እኔ ግን ልጆቼን አልሰጥም ሌላም ባል አላገባም ሌላም አልወልድም ብዬ ልጆቼን አሳደኩ። የሱን አደራ ጠብቄ ልጆቼን በሥነ ሥራዓት በማሳደግና ለቁም ነገር በማብቀቴ ለህገሬ ብድሬን መልሻለሁ” አሱም ለሠራተኛው ዓላማ ሞቷል። «እኔ ደግሞ ዕደለኛ ነኝ ዓለማዬ ሁሉ ተሳክቷል።» አሉና ውጤታማዋ  የቤተሰብ አርበኛ ወይዘሮ አልማዝ ገብሩ በድል አድራጊነት ፈገግታ።

**ማሳሰቢያ፦** የቦርድ አባለቱንና የመጽሔቱን አዘጋጆች ፩ኛ. አቶ ደምሴ ጽጌ ፪ኛ. አቶ ኃይለማርያም ፫ኛ. አቶ ታደሰ ማሞ ለቅንብራቸሁ በጣም አመሰገናችኋለሁ። የማርቆስን ሐሳስና የወይዘሮ ዳሯ ነጋሽን ታሪክ እንዲሁም የሠራተኛው ማኅበር ቀዳማዊ መሪው አበራ ገሙ (እኔ ጫማ አላደረግም ላብ አደሮቹ ጫማ ማረግ አሰከሚችሉ ድረስ ይል ነበር) አገሬ ብኖር ኖሮ ብዙ ነገሮችን ሰለነሱ እንዲሁም የሌሎቹን ቆራጥ መሪዎች እንደኔ በይሕወት የሌሉትን መጻፍ እችል ነበር ግን ስደት ላይ ሆንኩና አገሬ መጥቼ ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር ሆነ ከሚያውቋቸውም ጋር ተነጋገሮ ለመጻፍ አልተቻለም። በአሁን ጊዜ ደግሞ ዕድሜው እየገፋ መጥቷልና ያለን ጊዜ ጥቂት ነው። ሰለዚህ እኛ ባቀናባበረነው አንተ ምን አገባህ እንዳትሉኝ እኔም በበኩሌ አደራ እላችኋለሁ የመጻፍ መብታችሁን አከበረኩ ፤  አደነኩ አልተጋፈሁም።  በጥቂቱም ቢሆን ሳስበውና ስመኘው የነበረውን በከፊል እንደፈጽም አደረጋችሁኝ እንጂ። መልክቱ ለብዙዎቹ በተለይ የሠራተኛውን ትግልና መሠዋዕተነት ምን ያህል እንደከፈለበት ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲያወቀው በመፈለጌ ጭምር ነው። በዚህ አጋጣሚ ሰለ ሙዜየሙ መቋቋም/መከፈት በወያኔው በጸረ ኢትዮጵያ ዘመን በመሆኑ ግን ቅሬታ አለኝ። ይህ ብቻ አይደለም ብዙ ማርቆስ ሐሳሶችን በርሣ በነበሩበት ወቀት ከተኙበትና ከሻብያ ጋር በማበር ገለዋል ፤  አዲስ አበባም  እንደ ገቡ የዩኒቨርሰቲ ተማሪዎችና አሰተማሪዎች ፣ ጥቂት ቆይቶም  ደግሞ አሰፋ ማሩን ፣ ገ/እግዚአበሔር ኃይሌን(ኻይምን) ፣ ተስፋዬ ታደሰን ፣  ሽብሬ ደሳለኝን ፣ የአሥራ አምስትና የአሥር ዓመቱን ሕፃን ፤ ሰኔ ፲፱፻፷፯ና ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ከሁለት መቶ በላይ የተገደሉት  ከዚያም አልፎ ድፍን አገራችንን ከተቆጣጠሩ በኃላም ደግሞ በየጠቅላይ ግዛቱ

የገደላቸው ፣ የጨረሷቸው ፣ በሳት ያቃጠሏቸው ፣ ገደል የወረወሯቸው ሥማችው በሙዩዚይሙ የሚመዘገበት ቀን እሩቅ አይደለም።

## ድል ለሕዝባችን!!